


# የኢሕአግ ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በቀድሞ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላት መቋቋሙን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

በጀግኖች አባቶቻችን መስዋዕትነት ተጠብቃ የኖረችዉ ዉድ ሀገራችን ህልዉና በአደጋ ላይ ይገኛል:: ጸረ-ኢትዮጵያ በሆኑ የዉስጥና የዉጭ ሃይሎች አቀነባባሪነትና ሴራ በሀገርና በወገን ህልዉናና አንድነት ላይ ያነጣጠረ አደጋ ለመመከት ሀገር ወዳድ ሃይሎችና አርበኞች ዛሬም እንደ ትናንቱ ከባድ መስዋዕትነት በመክፈል ላይ ይገኛሉ::

እኛም በተለያየ ዓለም የምንገኝና የሀገራችን መጻኢ ዕድል የሚያሳስበን የቀድሞ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላት በጸረ-ወያኔ ትግሉ በግንባር ቀደምትነት በመዋደቅ ላይ ከሚገኘዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዓለምአቀፍ አከል ጋር በወቅታዊ የአገራችንና የግንባሩ እንቅስቃሴ ዙሪያ ሰፊ ዉይይትና የሃሳብ ልዉዉጥ በማድረግ የበኩላችንን ድርሻ መወጣት እንደሚገባን ከልብ በማመን የሚከተለዉን አቋም ወስደናል::

1. ዛሬ ሀገራችን ወያኔ/ኢሀአዴግ በሚያራምደዉ ኋላቀር ዘረኛ ፓሊሲ ሳቢያ መጠነሰፊ በሆነ የፓለቲከ፤የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ ቀዉስ ዉስጥ ተገኝለች:: ከዚህ ምስቅልቅል ችግር መዉጣት የሚቻለዉ ዘረኛዉና ወያኔ ከአጥፊ ፓሊሰዉ ጋር ከሥልጣን ሲወገድ ብቻ መሆኑን ተገንዘበናል:: ሥርዓቱ አስከልተወገደ ድረስ በሀገር ላይ የሚያስከትለዉ መዘዝ ቀላል አለመሆኑን በጥልቅ ተረድተናል::

2. ይህ በሰዉ ልጅ እኩልነት፤በሀገር አንድነትና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የማያምን ዘረኛና አምባገነናዊ ሥርዓት በሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር አምኖ የሕዝብን ድምጽ የማያከብር መሆኑን በታሪከዊዉ ምርጫ 97 ተረጋግጦአል:: ስለሆነም ይህን ጠመንጃ ነከሽ ዘረኛና አምባገነናዊ ስርዓት ለማስወገድ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የወሰደዉ የትጥቅ ትግል ስልት ትክክለኛና ወቅታዊ መሆኑን በማመን ከግንባሩ ጎን ተሰልፈን አቅማችን የፈቀደዉን ሁሉ ለማድረግ ቃል ገብተናል::

3. የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የሚዋደቅለት ዓላማ ቀደም ሲል የደምና የሕይወት መሰዋትነት የከፈልንበት የአገርን አንድነትና ህልዉና የማረጋገጥ ክቡር ዓላማ ስለሆነ፤የወያኔን ፋሺስታዊ አገዛዝ ለማስወገድ በሀገር ቤትም ሆነ በዉጭ አገር የሚኖሩ የቀድሞ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባላት ዛሬም እንደ ትናንቱ ለዉድ አገራቸዉ ሕልዉና ሲሉ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ጎን በመቆም የገቡትን ቃል ኪደን በማደስ እንዲንቀሳቀሱ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን::

4. የሀገርንና የወገን ደህንነትን መጠበቅ ሳይሆን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የአንድ አናሳ ስብስብ የሥልጣን ማስጠበቂያ መሣሪያ በመሆን በወገኑ ላይ ግፍ በመፈጸም ላይ የተሰማራዉ የመከላከያ ሠራዊት **ታሪክ ራሱን ከመድገሙ በፊት ግዜው ሳይመሽ** አቋሙን መርምሮ ከሕዝብ ጎን በመቆም ብሄራዊ ግዴታዉን እንዲወጣ እናስገነዝባለን::

5. ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ጎን ቆሞ የሚከሄደዉን መራራ ትግል በተቀናጀ መልክ ማገዝ እንደሚገባን በማመን፤እኛ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የምንገኝ የቀድሞ መከላከያ ሰራዊት አባላት «**የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር የቀድሞ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ**» ማቋቋማችን በታላቅ ኩራት እያበሰርን፤ ሌሎች የቀድሞ የትግል አጋሮቻችን ይህን ፈለግ በመከተል የቀድሞ አርማዉን እንዲያነሱ አገራዊና ወገናዊ ጥሪያችምም እናቀርባለን::

በዚህ አጋጣሚ ከእኛ ጋር ግንኙነት ማድረግ የሚፈልጉ የቀድሞ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላት በኢሜል ማለትም፤ eppfforce@gmail.com ሊደርሱን ይችላሉ::

## አንድነት ኃይል ነው!!

## የኢሕአግ የቀድሞ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አስተባባሪ ኮሚቴ

***መጋቢት 2001 (ማርች 2009)***

Email: info@eppfonline.org:  Website: www.eppfonline.org